# የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የወስጥ ደንብ ማሻሻያ ቁጥር 558/2013

## 1. መግቢያ

1.1 የተሻሻለዉን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የወስጥ ደንብ ቁጥር 554/2013ን (ከዚህ በኋላ "ደንብ" በመባል ይጠቀሳል) ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በማኘቱ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ (ከዚህ በኋላ "የምርት ገበያ" በመባል ይጠቀሳል) በምርት ገበያዉ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 550/1999 አንቀጽ 12(10) መሠረት ይህንን ደንብ ማሻሻያ አወጥቷል፡፡

1.2 ይህን የወስጥ ደንብ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" ተብሎ ይጠቀሳል) በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 አንቀጽ 6(3) በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት ካፀደቀዉ በኋላ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

1.3 ይህ የወስጥ ደንብ "የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የወስጥ ደንብ ማሻሻያ ቁጥር 558/2013" በመባል ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2 ማሻሻያ

የተሻሻለዉ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የወስጥ ደንብ ቁጥር 554/2013 (ከዚህ በኋላ "ደንብ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል) እንደሚከተለዉ እንደገና ተሻሽሏል፡፡

(1) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 2.1.2 በደንቡ አንቀጽ 2.1 ስር ተጨምሯል፡፡ ከንዐስ አንቀፅ 2.1.2 እስከ 2.1.64 የነበሩት ከንዐስ አንቀፅ 2.1.3 እስከ 2.1.65 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"2.1.2 ተቀጥያ ወይም እህት ከባንያ – ተቀጥያ ወይም እህት ከባንያ – አንድ ድርጅት በአንደኛው ድርጅት ስር ሆኖ የሚዋሯ ሲሆን ወይም ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ድርጅቶች በአንድ ሶስተኛ ድርጅት ስር ሆነው የሚዋሩ ሲሆን ወይም አንደኛው ድርጅት በሌላኛው ድርጅት ወስጥ ከ50 በመቶ በላይ የአክሲዮን ድርሻ ያለው ሲሆን ነው"

(2) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 2.1.59 ንኡስ አንቀጽ 2.1.60 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"2.1.60 የግብይት ክፍለ ጊዜ – በአንድ ወል ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ወሎች ላይ ግብይት የሚከሄደበት የተወሰነ ጊዜ ሲሆን ምርቱ የመጠበትን አካባቢ ወይም አካባቢዎች እና ምርቱ የሚቀመጥበትን የምርት ገበያው መጋዘን ወይም የተከለለ ጥበቅ የማቆያ ስፍራዎች እና ሌሎች በምርት ገበያው የሚወሰኑ ሁኔታዎችን ከግምት ወስጥ በማስገባት የሚወሰን ይሆናል፡፡"

(3) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 4.6.5.6 በደንቡ አንቀጽ 4.6.5 ስር ተጨምሯል፡፡ አንቀጽ 4.6.5.6 የነበረው 4.6.5.7 ሆኗል፡፡

"4.6.5.6 ማንኛውም አባል በበጀት አመቱ መጀመሪያ ላይ የአባልነት መቀመጫዉ እንዲሸጥለት በምርት ገበያው የሚዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ከጠየቀ እና በበጀት አመቱ ወስጥ በምርት ገበያዉ ላይ ግብይት ካላደረገ በስተቀር ዓመታዊ የአባልነት ክፍያ እንዲከፍል አይገደድም፡፡"

(4) የደንቡ ንዐስ አንቀጽ 4.8.1.3 (መ) ተሰርዝዋል፡፡

(5) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 4.8.1.4 በደንቡ አንቀጽ 4.8.1 ስር ተጨምሯል፡፡

"4.8.1.4 የአባልነት መቀመጫውን በጨረታ የሸጠ አባል ግዥው ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ መገበያት ማቆም አለበት፡፡"

(6) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 4.8.7 በደንቡ አንቀጽ 4.8 ስር ተጨምሯል፡፡ ከደንቡ ንዐስ አንቀፅ 4.8.7 እስከ 4.8.8 ያሉት ከንዐስ አንቀፅ 4.8.8 እስከ 4.8.9 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"4.8.7 በፍርድ ቤት ትእዛዝ በሃራጅ ስለሚሸጥ የአባልነት መቀመጫ

4.8.7.1 አንድ አባል በእዳ ምክንያት በምርት ገበያው ያለው የአባልነት መቀመጫ በፍርድ ቤት ትእዛዝ በሃራጅ እንዲሸጥ ሲወሰን የአባልነት መቀመጫው ሽያጭ በፍርድ አፈጻጸም አካል በኩል መሆን ይኖርበታል፡፡

4.8.7.2 ምርት ገበያው ለፍርድ አስፈጻሚው አካል ከአባልነት መቀመጫው ሽያጭ ጋር የተያያዙ አስፈላጊ መረጃዎችን ይሰጣል፡፡"

**(7)** የደንቡ ንዐስ አንቀጽ 4.9.1.2 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡ የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.9.1 ስር አዲስ ንኡስ አንቀጽ **4**.9.1.3 ተጨምሯል፡፡ አንቀጽ 4.9.1.3 የነበረው 4.9.1.4 ሆኗል፡፡

"**4**.9.1.2 ምክንያት ካልቀረበና ምክንያቱም በምርት ገበያው ተቀባይነት ካላገኘ በስተቀር፣ ማንኛውም አባል አባልነቱ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሶስት ወራት ወስጥ በምርት ገበያው መገበየየት ካልጀመረ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ከተገበየየ በኋላ በተከታታይ ለስድስት ወራት ያህል መገበየየት ካቋረጠ የሚሰጠው የሶስት ወራት ማስታወቂያ ጊዜ እንዳበቃ የምርት ገበያው አባልነቱን ማቋረጥ አለበት፡፡"

4.9.1.3 አባሉ ሊገበያይበት የሚችለው የምርት አይነት በምርት ገበያው በተለያየ ምክንያቶች እየተገበየየ ካልሆነ፣ አባሉ የግብይት ወኪል ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ሳይኖረው ሲቀር፣ አባሉ ግለሰብ ሲሆን በሞት ሲለይ እና ሌላ አባሉን ሙሉ በሙሉ መገበያየት እንዳይችል የሚያደርጉ የመሳሰሉት ምክንያቶች በንኡስ አንቀጽ 4.9.1.2 መሰረት ተቀባይነት የሚያራቸው ምክንያቶች ናቸው፡፡

**(8)** የሚከተሉት አዲስ ንኡስ አንቀጾች 4.9.5 እና 4.9.6 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.9 ስር ተጨምረዋል፡፡

"4.9.5 የአባልነት እወቅናው የተሰረዘበት አባል በምርት ገበያው ያለውን መቀመጫ የሚሸጥ መብት

የአባልነት እውቅናው የተሰረዘበት አባል በባለስልጣኑ መመሪያ መሰረት ለይግባኝ የተሰጠዉ ጊዜ ከተጠናቀቀበት ወይም ይግባኝ ካቀረበ ይግባኙ ወድቅ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሶስት ወራት ጊዜ ወስጥ የተሰረዘበት እውቅና እንዲመለስለት ለባለስልጣኑ አመልክቶ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደለት ወይም የአባልነት መቀመጫውን ለመሸጥ ለምርት ገበያው ካላመለከተ በስተቀር የአባልነት እውቅናው ከተሰረዘ ከሶስት ወራት በኋላ ለአባሉ በጽሁፍ የሶስት ወራት የቅድሚያ ማስታወቂያ በመስጠት በምርት ገበያው አመራር ወሳኔ መሰረት አባልነቱ ተቋርጦ የአባልነት መቀመጫውን ምርት ገበያው በራሱ በመሸጥ በደንቡ አንቀጽ 4.9.3.2 መሰረት ከሽያጩ የተገኘውን ገንዘብ እንዲመለስለት ያደርጋል፡፡

4.9.6 የአባልነት እውቅናው የታገደበት አባል በምርት ገበያው ያለውን መቀመጫ የመሸጥ መብት

የአባልነት እውቅናው የታገደበት አባል በባለስልጣኑ መመሪያ መሰረት ለይግባኝ የተሰጠዉ ጊዜ ከተጠናቀቀበት ወይም ይግባኝ ካቀረበ ይግባኙ ወድቅ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ባሉት በስድስት ወራት ጊዜ ወስጥ ለእውቅናው መታገድ ምክንያት የሆኑትን መስፈርቶች በማሟላት የአባልነት መቀመጫውን ካላስጠበቀ ወይም የአባልነት መመጫውን ለመሸጥ ለምርት ገበያው ካላመለከተ በስተቀር የአባልነት የእውቅና እገዳው ጊዜ እንዳበቃ ለአባሉ በጽሁፍ የሶስት ወራት የቅድሚያ ማስታወቂያ በመስጠት በምርት ገበያው አመራር ወሳኔ መሰረት አባልነቱ ተቋርጦ የአባልነት መቀመጫውን ምርት ገበያው በራሱ በመሸጥ በደንቡ አንቀጽ 4.9.3.2 መሰረት ከሽያጩ የተገኘውን ገንዘብ እንዲመለስለት ያደርጋል፡፡"

(9) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.10.1.1 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.10.1.1 ማንኛውም አባል ግብይቱን በተመለከተ እስከ አራት በሚደርሱ በተፈቀደላቸው የግብይት ተወካዮች የመወከል መብት ያለው ሲሆን በአንድ የግብይት ክፍል ጊዜ የገበያ ተሳትፎ ሊያደርግ የሚችሉት የግብይት ተወካዮች ግን ወካዩን ጨምሮ ከሁለት መብለጥ የለባቸውም፡ ምርት ገበያው በአንድ የግብይት ክፍለ ጊዜ ተሳትፎ የሚያደርጉ የገበያ ተወካዮችን ቁጥር አባላት ያላቸውን የግብይት ተሳትፎ፤ የሚገበያዩትን ምርት መጠን እና የሚያስተናግዱትን ደንበኞች መጠን ከግንዛቤ በማስተባት በግልፅ በሚቀመጥ አሰራር ሊያሻሽል ይችላል፡፡"

(10) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.14.3 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.14.3 እያንዳንዱ በጀት አመት ባበቃ በአራት ወር ጊዜ ወስጥ በምርት ገበያ በተዘጋጀው ቅፅ መሰረት በተመሰከረላቸው አዲተሮች የተመረመረ ሂሳብ መግለጫ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡"

(11) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.17.10.1.1 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.17.10.1.1 ማንኛውም አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ግብይቱን በተመለከተ በሁለት የግብይት ተወካይ ብቻ የመወከል መብት አለው። ሆኖም በአንድ የግብይት ክፍለ ጊዜ በግብይት መሳተፍ የሚችለው ራሱ ወካዩ ወይም አንድ ተወካይ ብቻ ነው፡ የተወከለው ሰው ከግብይት ጋር በተያያዘ ወኪል ለመሆን የሚፈቀድለት ለአንድ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ብቻ ነው፡"

(12) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 5.2.3 (መ) እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"5.2.3 (መ) ግብይት ማቆም – የምርት ገበያወን ግብይት ታአሚኒት እና ጤናማ ት ለማጠበቅ ወይም ለሌላ የደህንነት ምክንያት ሲባል ግብይቱ ከማጠናቀቁ/ከማዘጋቱ በፊት ግብይትን ማቆም ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ትእዛዝ ማስገባት፣ ማሻሻል ወይም ማሰረዝ አይፈቀድም፡፡"

**(13)** የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 5.2.4 በደንቡ አንቀጽ 5.2 ስር ተጨምሯል፡፡

"5.2.4 የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ ለሚደረግ የምርት ግብይት የኤሌክትሮኒክ የግብይት ክፍለ ጊዜ፤

እያንዳንዱ የኤሌክትሮኒክ ጨረታ ክፍለ ጊዜ የሚከተሉትን አምስት ንዑስ የግብይት ክፍለ ጊዜዎች ያካትታል፡፡

ሀ. ሻጭ ዋጋ የሚያስገባበት ንዑስ ክፍለ ጊዜ፡ በዚህ ንዑስ ክፍለ ጊዜ ሻጭ የመሸጫ ዋጋ ማስገባት ወይም ያስገባወን ትዕዛዝ ማሰረዝ ይችላል፡፡ ሻጭ የሚሰጠው ዋጋ የእለቱ የዋጋ ገደብ ካለ በዋጋ ገደቡ ወስጥ መሆን አለበት፡፡

ለ. ገዥው የጨረታ ዋጋ ትዕዛዝ የሚያስገባበት ንዑስ ክፍለ ጊዜ፡ በዚህ ንዑስ ክፍለ ጊዜ ገዥው የመግዣ ዋጋ ከማስገባት ባለፈ ያስገባወን ዋጋ ማሰረዝ የሚችል ሲሆን ማሻሻል ግን አይችልም፡ ገዥው የሚሰጠው ዋጋ የእለቱ የዋጋ ገደብ ካለ በዋጋ ገደቡ ወስጥ መሆን አለበት፡፡

ሐ. ገዥው ያስገባወን የጨረታ ዋጋ ትዕዛዝ ማሻሻል የሚችልበት ንዑስ ክፍለ ጊዜ፡ በዚህ ንዑስ ክፍለ ጊዜ ገዥው በቀደሞ ክፍለ ጊዜ ያስገባወን የዋጋ ትዕዛዝ ማሻሻል ይችላል፡፡ አዲስ ትዕዛዝ ማስገባት አይቻልም ነገር ግን ደጋግሞ ማሻሻል ይችላል፡፡ እያንዳንዱ የመግዣ ዋጋ ትዕዛዝ ማሻሻያ ቢያንስ በአንድ ብር መጨመር አለበት፡፡ ገዥው የሚሰጠው ዋጋ የእለቱ የዋጋ ገደብ ካለ በዋጋ ገደቡ ወስጥ መሆን አለበት፡፡

መ. ሻጩ የተሰጠዉን ዋጋ የሚቀበልበት ወይም የሚተዉበት ንዑስ ክፍለ ጊዜ፡ በዚህ ንዑስ ክፍለ ጊዜ ገዥው የሰጠው ዋጋ ሻጩ ከሰጠው ዋጋ ያነሰ ከሆነ ሻጩ በገዥ የተሰጠዉን ዋጋ መቀበል ወይም መተው አለበት፡፡

ሠ. ግብይቱ የሚጸምበት ንዑስ ክፍለ ጊዜ፡ ይህ ንዑስ ክፍለ ጊዜ በግብይት አሰራር ክፍል (back office) የሚጸም ሲሆን ሻጩ ለሸጥ የሚልግበትን ጥሩ ዋጋ ከሚጠ ወይም ከተቀበለ በኃላ የተዛመዱ ግብይቶች የሚጸመቡት ነው፡፡

ረ. በምርት ገበያው የሚወሰኑ ሌሎች ንዑስ የግብይት ክፍለ ጊዜዎች፡፡"

(14) የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 5.3.1.3 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"5.3.1.3 የመለያ ባጅ

ሀ. ማንኛዉም የመድረክ ወኪል በምርት ገበያው የተዘጋጀ የመለያ ባጅ ሁል ጊዜ በግልፅ በሚታይ አግባብ ሳያንጠለጥል እና የመገበያያ ጃኬት ሳይለብስ ወደ መገበያያ መድረኩ እንዲገባ አይፈቀድለትም፡

ለ. ማንኛውም የመድረክ ተወካይ ከምርት ገበያው በተለያዩ ምክንያቶች በሚገደብት፣ የማበያየት መብቱ በሚቋረጥበት ወይም ማበያየት እንዳችይል ሲደረግ የምርት ገበያውን መታወቂያ መመለስ ይገባዋል፡፡

ሐ. ማንኛውም የምርት ገበያው ሰራተኛ በምርት ገበያው የተዘጋጀ የመለያ ባጅ ሁል ጊዜ በግልፅ በሚታይ አግባብ ሳያንጠለጥል ወደ ማበያያ መድረኩ እንዲገባ አይፈቀድለትም።"

(15) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 5.3.1.5 የደንቡ አንቀጽ 5.3 ስር ተጨምሯል፡፡

"5.3.1.5 ተገበያዮች ወደ ግብይት መድረክ ከገቡ በኋላ እርስ በራሳቸው ማጋገር ክልክል ነው፡፡"

(16) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 5.4.2.1 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"5.4.2.1 በቃል የሚከተጋባት የግብይት ክፍለ ጊዜ ከማዘጋቱ በፊት ያለው የአንድ ደቂቃ ጊዜ ለእያንዳንዱ የግብይት ክፍለ ጊዜ እንደማዘጊያ ጊዜ ይቆጠራል። የግብይት አሰራር ተቆጣጣሪ ወይም የተመደበ የገበያው ሰራተኛ የመዝጊያ ጊዜው ሲጀምር የመጀመሪያውን የመዝጊያ ጥሪ እንዲሁም የግብይት ጊዜው ሲያበቃ የሚጨረሻውን የመዝጊያ ጥሪ ማሰማት አለበት። ምርት ገበያው እንደ ግብይቱ አይነት የማዘጊያ ጊዜው ሲጀምር የመጀመሪያውን የማዘጊያ ጥሪ እንዲሁም የግብይት ጊዜው ሲያበቃ የሚጨረሻውን የመዝጊያ ጥሪ የሚያሰማበትን ጊዜ ሊወስን ይችላል።"

(17) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 5.4.3.2 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"5.4.3.2 በግብይት ክፍለ ጊዜው ወስጥ ምንም ግብይት ካልተፈፀመ የማዘጊያ ዋጋው በሚጨረሻ የተመዘገበው ሚዛናዊ አማካኝ ዋጋ መሆን አለበት። ሆኖም በሚጨረሻ የተመዘገበው ዋጋ ሁለት ቀን ወይም ከዚያ በላይ ከቆየ የምርት ገበያው ተገቢ ነው ብሎ በገመተው ማጠን የዋጋ ገደብ ሊያስቀምጥ ይችላል።"

**(18)** የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 5.4.3.4 በደንቡ አንቀጽ 5.4.3 ስር ተጨምሯል፡፡

"5.4.3.4 ምርት ገበያው በአውቶማቲድ ስርዓት ዕለታዊ የዋጋ ተመን (daily price filter) የሚወሰንበትን አሰራር ይዘረጋል፡፡ ሆኖም ዕለታዊ የዋጋ ተመን በአውቶማቲድ ስርዓት መስራት ካልተቻለ በተለዩ ሁኔታዎች በእጅ ሊሰራ ይችላል፡፡"

(19) የደንቡ ንዐስ አንቀጾች 5.4.6.1 እና 5.4.6.2 እንደሚከተለዉ ተሻሽለዋል፡፡

"5.4.6.1 ዕለታዊ የአቋም ወሰን ባለባቸው ምርቶች ላይ የአንድ አባል ዕለታዊ የአቋም ወሰን አባሉ በአንድ የግብይት ቀን እንዲገዛ ወይም እንዲሸጥ የሚፈቀድለት በእያንዳንዱ ወል ወስጥ የተገለፀ ከፍተኛው ማጠን ነው

5.4.6.2 የተለየ ሁኔታ ሲፈጠር እና በጽሁፍ ተመዝግቦ በሚዋዝ ምክንያት፣ የምርት ገበያው ሜኔጅመንት፣ በተቻለ ፍጥነት ለዳይሬክተሮች ቦርድ እና ለምርት ገበያ ባለስልጣን በማሳወቅ እና ፣ ዕለታዊ የአቋም ወሰን ባለባቸው ምርቶች ላይ **በአንድ የግብይት ቀን** ወስጥ የነበረውን ዕለታዊ

የአቋም ወሰን ግብይት ከሚጸሙ በፊት ማለወጥ ይችላል። ለወጥ የተደረግበት ዕለታዊ የአቋም ወሰን የጊዜ ቆይታ በምርት ገበያው ሜጅመንት እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡”

(20) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 5.5.11 በደንቡ አንቀጽ 5.5 ስር ተጨምሯል፡፡ ከንዑስ አንቀፅ 5.5.11 እስከ 5.5.23 የነበሩት ከንዑስ አንቀፅ 5.5.12 እስከ 5.5.24 በሚል ተሸጋሽገዋል፡፡

“5.5.11 በቃል በማከተጋባት የግብይት መድረክ ላይ የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ የሚደረግ ግብይት

በቃል በማከተጋባት የግብይት መድረክ ላይ የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ የሚደረግ የምርት ግብይት፤ ግብይቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ሻጭ ባዶ የግብይት ትዕዛዝ ትኬት ጋድ ከምርት ገበያው በመቀበል የትዕዛዝ ትኬቱን ከሞላና ከፈረመ በኋላ የተሞላወን ትኬት በግብይት አሰራር መዝጋቢው በኩል አንዱን ቅጂ ለገዥ ማስጠት አለበት። ገዥው ሻጭ የፈረመውን የትዕዛዝ ትኬት በማየት በፊርማው ማጽደቅ አለበት፡፡ የትዕዛዝ ትኬቱ የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ) ቀን

ለ) የትእዛዝ ትኬት ቁጥር

ሐ) የሻጭ የሚከማቻ መጋዘን ደረሰኝ ቁጥር

መ) የምርቱን ደረጃ ምልክት

ሠ) ማጠን

ረ) ዋጋ

ሰ) የሻጭ አባል መለያ ቁጥር

ሸ) የሻጭ ደንበኛ መለያ ቁጥር

ቀ) የሻጭ መድረክ ተወካይ መለያ ቁጥር

በ) የሻጭ ፊርማ

ተ) የገዥ አባል መለያ ቁጥር

ቸ) የገዥ መድረክ ተወካይ መለያ ቁጥር

ነ) የገዥ ደንበኛ መለያ ቁጥር

ኘ) የገዥ ፊርማ”

(21) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 5.5.19.2 (ሐ) (i) እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

“i. ትዕዛዙን በዚያኑ ዕለት (የግብይት ክፍለ ጊዜው ካላበቃ) ወይም በሚቀጥለው የግብይት ቀን በገበያ ሚፀምና ስህተቱ ባይከሰት ኖሮ ደንበኛው የተሻለ ዋጋ ያገኝ ከነበረ የደንበኛውን የባንክ ሂሳብ ማስተካከል፤”

(22) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 5.7.1 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"5.7.1 የተፈፀሙ ግብይቶች ህልውናና ጤናማነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል እና ለህዝብ ይፋ የሚደረግ የግብይት ሚዛን ከነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ከሆነ ይህን ለማስተካከል ምርት ገበያው ግብይቶችን ሊሰርዝ ይችላል፡፡ ይህ እርምጃ ሊወሰድ የሚችለው የምርት ገበያውን የግብይት መድረክ አግባብ ባልሆነ ወይም በተሳሳተ አጠቃቀም ወይም በሲስተም ማብላሸት ምክንያት ግብይት የሚዛናጉ ሁኔታዎችን ለማስተካከል ነው፡፡ የገበያውን ህልውና እና ጤናማነትን የሚዛናጉ ግብይቶችን ምርት ገበያው ሊሰርዛቸው ይችላል፡፡"

(23) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 5.7.2 በደንቡ አንቀጽ 5.7 ስር ተጨምሯል፡፡ የደንቡ ንዐስ አንቀጽ 5.7.2 የነበረው ንዐስ አንቀጽ 5.7.3 በሚል ተሸጋሽጓል፡፡

"5.7.2 ግብይት ለማሰረዝ የተወሰኑ ወሳኔዎች በሙሉ ለምርት ገበያው ቦርድ እና ለባለስልጣኑ ወዲያውኑ ወይም እጅግ ቢዘገይ ግብይቶች ከተሰረዙበት ቀጥሎ ባለው የስራ ቀን ሪፖርት መደረግ አለባቸው፡፡"

(24) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 6.4.1 (ለ) በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 6.4.1 ስር ተጨምሯል፡፡ እንዲሁም የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 6.4.1 የነበረዉ 6.4.1(ሀ) ሆኗል፡፡

"6.4 የተከለከሉ ግብይቶች

6.4.1(ለ) የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ ለሚደረግ የምርት ግብይት የአንድ ገዢ አባል ሁለት የመድረክ ተወካዮች በአንድ የሚከማቹ መጋዘን ደረሰኝ ቁጥር ለተመሳሳይ ደንበኛ ለመግዛት መወዳደር ክልክል ነው፡፡"

(25) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 6.4.7 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 6.4 ስር ተጨምሯል፡፡

"6.4.7 ስለተቀጥያ ድርጅቶች ግብይት

6.4.7.1 በምርት ገበያው ግብይት የሚፈጽሙ በአንድ ድርጅት ሥር ያሉ ተቀጥያ ወይም እህትማማች ድርጅቶች ግብይት በምርት ገበያው የሚዘጋጀውን ቅጽ አንድ ጊዜ በመሙላት ይህንኑ ለምርት ገበያው ማሳወቅ ያለባቸው ሲሆን በቀጣይ ለውጥ ሲኖርም በተመሳሳይ ሁኔታ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

6.4.7.2. በአንድ ድርጅት ሥር ያሉ ተቀጥያ ወይም እህትማማች ድርጅቶች በምርት ገበያው ግብይት በሚፈጽሙበት ወቅት በአቅርቦትና ፍላጎት ማጠን ብቻ የሚወሰነውን የገበያ ዋጋ የማግኛ ዘዴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማድረስ የለባቸውም፡

6.4.7.3 በአንድ ድርጅት ሥር ያሉ ተቀጥያ ወይም እህትማማች ድርጅቶች ከላይ በአንቀጽ 6.4.7.1 እና 6.4.7.2 የተደነገገውን ተላልፈው ግብይት ከፈጸሙ ምርመራ በማድረግ ቅጣት ሊጣልባቸው ይችላል፡፡"

(26) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 6.4.8 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 6.4 ስር ተጨምሯል፡፡

"6.4.8 በቀጥታ ግብይት ትስስር ለሚገበያዩ አቅራቢዎች ስለሚሰጥ አገልግሎት

6.4.8.1 በቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1051/2010 እንዲሁም አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ እና መመሪያ መሰረት በቀጥታ ግብይት ትስስር አማራጭ ለማበያየት ህጋዊ የሆነ ወል ሚድረጋቸውን የሚያሳይ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ ማስረጃ ይዘው የሚቀርቡ ተገበያዮች በሚጠይቁበት ጊዜ፤ ምርት ገበያው ለቀረበው ምርት የጥራት ደረጃ በመመደብ፣ የምርቱን አይነት እና የምርቱን ጥቅል ክብደት ከነሚኪናው በመመዘን ማዘግቦ መረጃ ይሰጣል፡፡

6.4.8.2 የምርት ጥራት ደረጃን በተመለከተ አቅራቢዎች ቅሬታ ካላቸው በቡና እና ሻይ ልማትና ግብይት ባለስልጣን ሥር ለሚገኘው የቡና ጥራትና ቁጥጥር ማእከል ቅሬታቸውን ማቅረብ ይችላሉ፡፡

6.4.8.3 ምርት ገበያው በዚህ አንቀጽ ማሰረት ለሚሰጠው አገልግሎት ተመጣጣኝ ክፍያ ያስከፍላል፡፡

6.4.8.4 ምርት ገበያው በአንቀጽ 6.4.8.1 ማሰረት ምርት ገበያው የሚሰጠውን አገልግሎት ለማገኘት የሚመጣን ምርት ሙሉ መረጃ ማዘግቦ መያዝ አለበት፡፡"

(27) የደንቡ ንኡስ አንቀጾች 6.5(መ) እና 6.5(ሠ) እንደሚከተለዉ ተሻሽለዋል፡፡ የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 6.5 ስር አዲስ ንኡስ አንቀጽ 6.5(ረ) ተጨምሯል፡፡ ንኡስ አንቀጽ 6.5(ረ) የነበረዉ 6.5(ሰ) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

"መ. የአባሉ ወይም የግብይት ወኪሉ የማበያየት መብቱ ካልታገደ፣ ለማበያየት ከተሰጠው የንግድ ፈቃድ ውጭ ከሚፈጠው የግብይት ወገን ውጭ እና የተገበያይ አይነት ውጭ ለማበያየት የጠየቀ እና በስሩም ማበያት የሚችሉ ደንበኞች ካሉ፣ እንዲሁም በምርት ገበያው በሆኑ ሌሎች ምክንያቶች ሙሉ በሙሉ ማበያየት ያልቻለ ካልሆነ በስተቀር በሌላ መደበኛ አባል ወይም የዚሁ መደበኛ አባል ሰራተኛ ወይም

ሠ. የአባሉ ወይም የግብይት ወኪሉ የማበያየት መብቱ ካልታገደ፣ ለማበያየት ከተሰጠው የንግድ ፈቃድ ውጭ ከሚፈጠው የግብይት ወገን ውጭ እና የተገበያይ አይነት ውጭ ለማበያየት የጠየቀ እና በስሩም ማበያት የሚችሉ ደንበኞች ካሉ፣ እንዲሁም በምርት ገበያው በሆኑ ሌሎች ምክንያቶች ሙሉ በሙሉ ማበያየት ያልቻለ ካልሆነ በስተቀር ወሰን አባሉ ሊገበያይ በሚችልበት ምርት ወሰን አባል ወይም የዚሁ ወሰን አባል ሰራተኛ ወይም

ረ. አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ወይም የግብይት ወኪሉ የማበያየት መብቱ ካልታገደ፣ ለማበያየት ከተሰጠው የንግድ ፈቃድ ውጭ ከሚፈጠው የግብይት ወገን ውጭ እና የተገበያይ አይነት ውጭ ለማበያየት የጠየቀ እና በምርት ገበያው በሆኑ ሌሎች ምክንያቶች ሙሉ በሙሉ ማበያየት ያልቻለ ካልሆነ በስተቀር አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ወይም የዚሁ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ሰራተኛ ወይም፤"

(28) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 7.25.1 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"7.25.1 የወል ማካሻያ ሃሳብ አቀራረብ

7.25.1.1 የወል ማሻሻያ ሃሳብ ከምርት ገበያው ፍላጎት ወይንም ከምርት ገበያው ውጭ ባሉ አካላት ፍላጎት ሊመነጭ ይችላል፡፡

7.25.1.2 የሚመለከተው የምርት ገበያው የስራ ክፍል የአንድን ምርት መመዘኛ እና ደረጃ የሚመጣ ወይም የማሻሻል አስፈላጊነት ላይ ጥናት በማድረግ የደረሰበትን መደምደሚያ ለምርት ገበያው ሜጅመንት ማቅረብ እንዲሁም ሂደቱን ማስተባበር አለበት፡፡

7.25.1.3 በዚህ አንቀጽ 7.25.1.2 መሰረት የቀረበው ጥናት እና የተደረሰበት መደምደሚያ በምርት ገበያው ሜጅመንት ሲጸድቅ በደንቡ አንቀጽ 7.25.2 መሰረት ለተቋቋመው የቴክኒክ ቡድን (ከዚህ በኋላ "የቴክኒክ ቡድን" እየተባለ ይጠቀሳል) ለዝርዝር ጥናት መቅረብ አለበት፡፡"

(29) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 7.25.2 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"7.25.2.1 የቴክኒክ ቡድኑ የሚከተሉትን አባላት ይኖሩታል

i) ለቡና

ሀ) ከምርት ገበያው የተወከሉ ከሁለት እስከ ሶስት ለሚሆኑ የቡና ጥራት ባለሙያዎች (አንደኛው ሰብሳቢ ይሆናል)፣

ለ) ከኢትዮጵያ ቡና እና ሻይ ልማት እና ግብይት ባለስልጣን የሚወከል አንድ የቡና ጥራት ባለሙያ

ሐ. ከኢትዮጵያ ቡና ላኪዎች ማህበር የሚወከል አንድ የቡና ጥራት ባለሙያ

መ. ከብሄራዊ ግብይት ፈጻሚዎች ማህበር የሚወከል አንድ የቡና ጥራት ባለሙያ

ሠ. እንደ አስፈላጊነቱ በምርት ገበያው የሚሰየም የሌላ አግባብነት ያለው ተቋም አንድ የቡና ጥራት ባለሞያ

ii) ከቡና ውጭ ላሉ ምርቶች

ሀ) ከምርት ገበያው የተወከሉ ከሁለት እስከ ሶስት ለሚሆኑ አግባብነት ያለው ምርት ጥራት ባለሙያዎች (አንደኛው ሰብሳቢ ይሆናል)፣

ለ) ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት የሚወከል አንድ አግባብነት ያለው ምርት ጥራት ባለሙያ

ሐ) ከኢትዮጵያ የጥራጥሬ፣ የቅባት እህሎች እና ቅመማቅመም አቀናባሪዎች እና ላኪዎች ማህበር የሚወከል አንድ አግባብነት ያለው ምርት ጥራት ባለሙያ

መ) ከብሄራዊ ግብይት ፈጻሚዎች ማህበር የሚወከል አንድ የቡና ጥራት ባለሙያ

ሠ) እንደ አስፈላጊነቱ በምርት ገበያው የሚሰየም የሌላ አግባብነት ያለው ተቋም አንድ አግባብነት ያለው ምርት ጥራት ባለሙያ፡፡

7.25.2.2 የቴክኒክ ቡድኑ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

7.25.2.3 ከአባላት ሁለት ሶስተኛው ከተገኙ ምልዓተ–ጉባኤ ይሆናል፡፡

7.25.2.4 የቴክኒክ ቡድኑ ውሳኔዎች በስብሰባው በተገኙ አባላት በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፡፡ ሆኖም ድምጽ እኩል በኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

7.25.2.5 የቴክኒክ ቡድኑ የምርት መመዘኛ ለማውጣት በሚያስፈልግ ጊዜ ለተከታይ ማሻሻያዎች አገልግሎት ይሰጣል፡፡

7.25.2.6 የቴክኒክ ቡድኑ የምርት ደረጃ እና ክፍፍልን ቴክኒካዊ ጉዳዮች በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከተው የምርት ገበያው የስራ ክፍል በጽሁፍ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ አለበት፡፡ ጉዳዩ በጽሁፍ የቀረበለት የሚመለከተው የምርት ገበያው መምሪያ በጽሁፍ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ለቀጣይ ድጋፍ ለኢንዱስትሪ ምክክር ጉባኤ ማቅረብ አለበት፡፡"

(30) የደንቡ ንዑስ አንቀፅ 7.25.3 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"7.25.3 ለስልጠና፣ ምርምርና የግብይት ማስፋፍያ መምሪያ ከቴክኒክ ቡድኑ በተሰጠው ቴክኒካዊ የውሳኔ ሃሳብ ላይ የገበያ ትንታኔ በማካናወን የግብይት ወል ረቂቅ ማዘጋጀት አለበት፡፡"

**(31)** የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 7.25.4 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"7.25.4 የግብይት ወል ረቂቁ ለዚሁ ወል ተብሎ ለሚደራጀው የኢንዱስትሪ ምክክር ጉባኤ መቅረብ አለበት፡፡"

**(32)** የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 7.25.5 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"7.25.5 በምርት ገበያው መደበኛ ጥሪ የሚቀረው የኢንዱስትሪ ምክክር ጉባኤ የሚከተሉትን አባላት ማካተት አለበት፡፡

ሀ. አስር እና ከዛ በላይ የሆኑ አምራቾች እና ሻጮችን ከሚወክሉ ሕጋዊ እወቅና ካላቸው የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ማህበራት ወይም ሌሎች ድርጅቶች የተወጣጡ ተወካዮች፣

ለ. አስር እና ከዛ በላይ የሆኑ ላኪዎችን፣ ነጋዴዎችን እና አዘጋጆችን ከሚወክሉ ሕጋዊ እወቅና ካላቸው የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ማህበራት ወይም ሌሎች ድርጅቶች የተወጣጡ የተወሰነ ምርት ገዢዎች ተወካዮች፣

ሐ. ከዚህ በላይ በንኡስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) ስር በተመለከተው አኳኃን ከአስር በላይ ተወካዮች የሚኔተፉ ከሆነ ወክልናው ተመጣጣኝ መሆን አለበት፣ እና

መ. ሕጋዊ እወቅና ያላቸው የኢንዱስትሪ ማህበራት ወይም ወካይ ተቋማት ከሌሉ የሚመለከተው የምርት ገበያው የስራ ክፍል የንግድ ዘርፉን በመተንተን አግባብነት ላለው ተወካይ በምርት ገበያው ጥሪ እንዲደረግ ለውሳኔ ማቅረብ አለበት፡፡"

**(33)** ከ7.25.6 እስከ 7.25.12 ያሉት የደንቡ ንኡስ አንቀጾች ከ7.25.6 እስከ 7.25.13 ሆነው ተሸጋሽገው እንደሚከተለዉ ተሻሽለዋል፡፡ ንዑስ አንቀፅ 7.25.13 እስከ 7.25.14 የነበሩት ከንዐስ አንቀፅ 7.25.14 እስከ 7.25.15 በሚል ተሸጋሽገዋል፡፡

"7.25.6 የደንቡ ንዐስ አንቀጽ 7.25.5 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ማህበራት ተወካዮች ምርጫ የሚከናወነው የማህበራቱን ወክልና ማስረት በማድረግ መሆን አለበት፡፡

7.25.7 የኢንዱስትሪ ምክክር ጉባኤ ብቸኛ ዓላማ ረቂቅ ወሉን መመርመር እና የጽሁፍ አስተያየት ለምርት ገበያው መስጠት ይሆናል፡፡

7.25.8 የሚመለከተው የምርት ገበያው የስራ ክፍል ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የምርት ገበያው የስራ ክፍሎች ጋር በመመካከር እንዲሁም ከቴክኒካል ቡድን እና ከኢንዱስትሪ ምክክር ጉባኤ ያገኘውን የጥናት ሰነድ መሰረት በማድረግ ወል በማዘጋጀት ለምርት ገበያው ሜጅመንት እንዲጸድቅ ያቀርባል፡፡

7.25.9 የተዘጋጀውን ወል በምርት ገበያው ሜጅመንት ሲጸድቅ የሚመለከተው የምርት ገበያው የስራ ክፍል ወሉን የሜጩሻ ቅርጽ በማስያዝ ከሕግ አንጻር እንዲፈተሸ ለሕግ ማስከበሪያ መምሪያ ማቅረብ አለበት፡፡ የሕግ ማስከበሪያ መምሪያ የሜጩሻ ቅርጽ የያዘውን ወል ለምርት ገበያው ቦርድ ወሳኔ ማቅረብ አለበት፡

7.25.10 የሕግ ማስከበሪያ መምሪያ የምርት ገበያውን ቦርድ ይሁንታ ካገኘ በኋላ ወሉን እንዲያጸድቀው ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ማላክ አለበት፡፡

7.25.11 የምርት ገበያው ለባለስልጣኑ እንዲጸድቅ ከሚልከው ወል ጋር ወሉን አስመልክቶ የተደረገ ጥናት አጭር መግለጫ እንዲሁም ቴክኒካል ቡድን እና የኢንዱስትሪ ምክክር ጉባኤ ከወሉ ጋር በተያያዘ የሰጡትን አስተያየት ያካተተ አጠቃላይ ሪፖርት አባሪ አድርጎ ማቅረብ አለበት፡፡

7.25.12 የሕግ ማስከበሪያ መምሪያ የጸደቀውን ወል ለዋቢነት ማስቀመጥ እና በሚያስፈልግበትም ጊዜ ለሚፈልገው አካል መስጠት አለበት፡፡

7.25.13 የተሻሻለው ደንብ አንቀጽ 7 አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ከላይ በንዐስ አንቀጽ 7.25 ስር የተቀመጡት ድንጋጌዎች ቀደም ሲል የጸደቁ ወሎችን ለማሻሻልም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡"

(34) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 10.6.1 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 10.6 ስር ተጨምሯል፡፡ ንዐስ አንቀፅ 10.6.1 እስከ 10.6.2 የነበሩት ከንዐስ አንቀፅ 10.6.2 እስከ 10.6.3 በሚል ተሸጋሽገዋል፡፡

"10.6.1 የክፍያ ሚፈጸሚያ ቀን

በምርት ገበያው በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በቀር፤ በምርት ገበያው ለሚደረግ ግብይት የክፍያ ሚፈጸሚያ ቀን ከህዝብ የበዓል ቀን ውጭ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ይሆናል፡፡"

(35) ንዑስ አንቀፅ 10.6.1 የነበረው ንዑስ አንቀፅ 10.6.2 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"10.6.2 የአባላት የተጣራ ግዴታ መግለጫ

10.6.2.1 የክፍያና ርክብክብ ሚፈፀሚያ በአባላት የተፈጸመ ግብይትንና በክፍያና ርክብክብ ሚፈጸሚያ የተዛመደን ግብይት መሠረት በማድረግ የክፍያ ሚፈጸሚያ ክፍል የአባላትን የተጣራ ግዴታ መግለጫ ማዘጋጀትና ከግብይቱ ቀን ቀጥሎ ባለው የክፍያ ሚፈጸሚያ ቀን ከጥዋቱ 2፡00 ሰዓት ላይ እያንዳንዱ አባል ስለ መግዣ ገንዘብ ማስገቢያ እና የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሣቦች አስሜልክቶ ያለበትን ግዴታ ለአባላቱ ማሳወቅ አለበት። በአባላት የተጣራ ግዴታ ላይ የተሰጠው መግለጫ በአባላት ላይ አስገዳጅነት አለው።

10.6.2.2 ተገበያይ አባላት፣አገናኝ አባላት ፣ክፍያ ፈጻሚ ገዥ-ብቻ ወሰን ተገበያይ አባላት እና ሻጭ-ብቻ ወሰን ተገበያይ አባላት እና አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ በእያንዳንዱ የግብይት ቀን ማግስት በሚኝ የክፍያ ሚፈጸሚያ ቀን የክፍያና ርክብክብ ሚፈጸሚያ ማዕከያ የሚሰጠውን የተጣራ የግዴታ መግለጫ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው። የምርት ገበያው የተጣራ የግዴታ መግለጫ ለአባላት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በማጓገዝ ለሜላክ ይችላል፡፡"

(36) ከንዑስ አንቀፅ 10.6.2 የነበረው ንዑስ አንቀፅ 10.6.3 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"10.6.3 ደህረ ንግድ ክፍያ አፈፃፀም

10.6.3.1 ስለ ገንዘብ ዝውውር

የክፍያ ርክብክብ ሚፈጸሚያ ማዕከያ ስለ አባላት የመግዣ ገንዘብ ከአባላት የመግዣ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ወይም ተፈጻሚ የሚሆን ከሆነ ከአባላት ደንበኛ የመግዣ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ወይም ከአባላት የክፍያ ሚፈጸሚያ የመግዣ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ የተጣራ የሽያጭ ክፍያ/ግዴታ ከግብይቱ ቀን ቀጥሎ ባለው የክፍያ ሚፈጸሚያ ቀን ከጥዋቱ 2፡00 እስከ 3፡00 ሰዓት ድረስ በወጪ ተከፋይ ማዛዝ አለበት።

10.6.3.2 የምርት ገበያው ከግብይቱ ቀን በኋላ ባለው የክፍያ ሚፈጸሚያ ቀን ከጥዋቱ 5፡00 እስከ 6፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ወስጥ አባላት ያለባቸውን የተጣራ የሽያጭ ግዴታ/ክፍያን ወደ ተገበያይ አባላት እና አገናኝ አባላት ወይም ተፈጻሚ የሚሆን ከሆነ ወደ አገናኝ አባላት ደንበኞች ወይም ወደ ወሰን አገናኝ አባላት ወይም ወደ ሻጭ ብቻ ወሰን ተገበያይ አባላት የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳቦች ገቢ ማድረግ አለበት።

10.6.3.3 ክፍያ ሚፈጸሚያ ተቋም የአባላት የተጣራ የግዴታ ማለጫ መሠረት አድርጎ ከንግዱ ቀን ቀጥሎ ባለው የሥራ ቀን የአባላት ደንበኞች የርክክብ ማስታወቂያን ማዘጋጀትና ለምርት ገበያው ንግድ የሚሆኑ ምርቶችን ለማስረከብ በማከማቻ መጋዘን ጨረታ ላይ ለሚተፉ እያንዳንዳቸው አባላት ወይም ደንበኞች ማስጠት አለበት። የርክክብ ማስታወቂያው በአባላትና ደንበኞች ላይ አስገዳጅነት አለው።"

(37) የደንቡ ንኡስ አንቀጾች 11.3.4 እና 11.3.6 እንደሚከተለዉ ተሻሽለዋል፡፡

"11.3.4 የማከማቻ ደረሰኙ የተጠቀሰዉን የምርት ርክክብ ቀነ ገደብ ጊዜ አብቅቶ የተከማቹት ምርቶች ካልተወሰዱ፣ ማከማቻ መጋዘኑ የተከማቸዉን ምርት እንደገና ደረጃ የማውጣትና ማእከላዊ ማከማቻም ዘግይቶ የሚከብ ክፍያዎችን ማሰብሰብ አለበት።

11.3.6 በማከማቻ ደረሰኙ የተጠቀሰው የምርት ርክክብ ቀነ ገደብ ጊዜ አብቅቶ የተከማቹት ምርቶች ካልተወሰዱ ማእከላዊ ማከማቻ ሁለት ማስጠንቀቂያዎችን በጽሁፍ ለገዢው ይሰጠዋል። እነዚህም ማስጠንቀቂያዎች የሚሰጡት አንደኛዉ እንደ ምርቱ ወል አይነት የምርቱ የሚከቢያ ጊዜ ለማለቅ አጋማሽ ጊዜ ሲቀረው ሲሆን ሌላኛዉ ደግሞ ክምችቱ ከመሸጡ አምስት ቀናት ቀድሞ ይሆናል።"

(38) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 14.3.2 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል

"14.3.2 አባሉ ከአዲስ ደንበኛው ጋር ግንኙነት ሲመሠርት፣ የደንበኛውን የኋላ ታሪክ፣ ሐቀኝነት፣ የፋይናንስ ብቃቱንና የኢንቨስትመንት ዕቅዶቹን፣ የደንበኛውን የግብር እዳ የሌለበት ስለመሆኑ የሚያሳይ ሚረጃ እንዲያቀርብ በማጠየቅ ተገቢዉን እርምጃ መዉሰድ እንዲሁም በምርት ገበያው ከደንበኛው ጋር ባለው ግንኙነት ወቅታዊዉን የግብይት ተገቢ ዋጋ እና ግብይትን ወይም በምርት ገበያው የተሰጠዉን የትዕዛዝ ብዛት ጨምሮ የምርት ገበያው ከተቀማጭ ሂሣብ፣ ከዋጋ ብዛት ጋር የተያያዙ የግብይት ገደቦችን የተመለከቱ አግባብነት ያላቸዉን ጠቃሚ ሚረጃዎች በበቂ ሁኔታ ማወቅ አለበት።"

(39) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 14.8.3 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል

"14.8.3 ማንኛዉም አባል የኦዲት ምርመራ የተደረገበትን የሂሣብ መግለጫ እና ሪፖርት የአባሉ የበጀት ዓመት በተጠናቀቀ ከአራት ወራት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ለምርት ገበያው ማቅረብ ይኖርበታል። ሆኖም የምርት ገበያው የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜዉን ለማራዘም በቂ ምክንያቶች አሉ ብሎ ካመነ፣በቂ ነው ብሎ ለሚያስበው ጊዜ የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜዉን ማራዘም ይችላል።"

(40) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 15.2.3.1 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል

"15.2.3 ሦስተኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋቶች የሚከተሉትን ጥፋቶች ያጠቃልላል፡፡

**15.2.3.1** ንዑስ አናቅፅ 4.5.5፣ 4.5.6፣ 4.5.11፣ 4.5.14፣ 4.6.3.2፣ 4.11፣ 4.12.1፣ 4.12.5፣ 5.4.4.1፣ 5.4.6.1፣ 5.5.1.4፣ 5.5.5፣ 5.5.8.5፣ 5.5.8.6፣ 5.5.17፣ 6.3፣ 6.4፣ 6.6፣

8.2.2፣ 10.5፣ 14.1፣ 14.2፣ 14.3፣ 14.4፣ 14.5፣14.6፣ 14.7፣ 14.8 ወይም 17.2.3 በመተላለፍ የተፈጸሙ ድርጊቶች ወይም"

**(41) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.1.3.3 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል**

"16.1.3.3 በተከራካሪ ወገኖች በተለየ ሁኔታ የሚወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማመልከቻው በቀረበበት ቀን ክርክሩ ወይም አለመግባባቱ የተነሳበት ጉዳይ በገንዘብ ሲተመን ከብር 250,000 /ሁለት መቶ ሃምሣ ሺህ/ የሚበልጥ ከሆነ ሦስት የግልግል ዳኞች በሚሰየሙበት ጉባኤ እንዲታይ ይመራል። እንዲሁም ክርክሩ ወይም አለመግባባቱ የተነሳበት ጉዳይ በገንዘብ ሲተመን ከብር 250,000 /ሁለት መቶ ሃምሣ ሺህ/ የማይበልጥ ከሆነ ጉዳዩ በአንድ የግልግል ዳኛ እንዲታይ ይመራል።"

(42) የደንቡ አንቀጽ 16.1.4 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"16.1.4 ዕርቅ

16.1.4.1 ተከራካሪ ወገኖች በቀጥታ ወደ ግልግል ዳኝነት የመሄድ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በተከራካሪ ወገኖች መካከል ያለመግባባት ሲፈጠር እና አቤቱታ ሲደርሰው የሚመለከተው የምርት ገበያው ሰራተኛ ጉዳዩን ተመልክቶ ተከራካሪ ወገኖቹን በመጥራት ጉዳያቸውን በሚጠቻው አስታራቂዎች በእርቅ እንዲጨርሱ ጊዜ ወስኖ ይነግራቸዋል፡፡ በተሰጣቸው ጊዜ ወስጥ ጉዳያቸውን በእርቅ ጨርሰው የታረቁበትን የጽሁፍ ማስረጃ ወይም ስምምነት ሲያቀርቡ የሚመለከተው የምርት ገበያው ሰራተኛ ጉዳዩ በእርቅ ሚጸመን አረጋግጦ መዝገቡን ይዘጋል፡፡

16.1.4.2 በተከራካሪ ወገኖች መካከል የተፈጠረው ያለመግባባት በአንቀጽ 16.1.4.1 ማሰረት በእርቅ ያላለቀ ከሆነ የሚመለከተው የምርት ገበያው ሰራተኛ በምርት ገበያው ደንብ ማሰረት ጉዳዩን ወደ ግልግል ዳኝነት ይመራዋል፡፡

16.1.4.3 የእርቅ ሂደቱ ሳይሳካ ከቀረ፣ አስታራቂ ወይም አስታራቂዎች የነበሩ በዚሁ ተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የግልግል ዳኞች ሆነው ሊሾሙ አይችሉም።"

(43) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 16.1.28 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.1 ስር ተጨምሯል፡፡

"16.1.28 የግልግል ዳኝነት ወሳኔን ስለሚፈጸም

16.1.28.1 ምርት ገበያው በግልግል ዳኛ/ዳኞች የተሰጠውን ወሳኔ በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ እንደ ፍርዱ እንዲፈጸም ለፍርድ ባለእዳው በጽሁፍ ያሳወቃል፡፡

16.1.28.2 በግልግል ዳኛ/ዳኞች የተሠጠውን ወሳኔ የፍርድ ባለእዳው በአንቀጽ 16.1.25.1 ማሰረት በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ እንደ ፍርዱ ካልተፈጸመ በደንቡ አንቀጽ 4.7.1.5 ማሰረት ከአባልነት ይታገዳል፡፡"

(44) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"16.2.2 በበና ደረጃ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ ሥነ-ስርዓት

በቡና እና ሻይ ልማትና ግብይት ባለስልጣን ሥር የሚገኘው የቡና ጥራትና ቁጥጥር ማእከል (ከዚህ በኋላ የጥራት ቁጥጥር ማእከል ተብሎ በሚጠራዉ) ከቡና ጥራት ጋር በተያያዘ በምርት ገበያው እና በገዢ ወይም በአስቀማጭ መካከል የሚነሳ ክርክርን በሚከተሉት ድንጋጌዎች መሰረት ይወስናል። የቡና ጥራት ደረጃ ወደ አገር ወስጥ ደረጃ ዝቅ እንዲደረግ በበና አስቀማጭ ወይም ገዥ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረወም።"

(45) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.1.2 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"16.2.2.1.2 ያለመግባባቶችን በቅድሚያ በወይይት/በድርድር ለመፍታት የሚደረግ ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ; የቡና ጥራትን በተመለከተ በምርት ገበያዉ ላይ ቅሬታ ማቅረብ የሚፈልግ ማናቸዉም አስቀማጭ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካላቃተዉ በስተቀር ቅሬታዉን ለቅሬታዉ ምክንያት የሆነዉን በምርት ገበያው የተሰጠዉን ወሰኔ ባወቀ በ24 ሰዓት ወስጥ ለቡና ጥራት ቁጥጥር ማእከል ማቅረብ ይኖርበታል። የቅሬታ አቤቱታው በምርት ገበያው የተዘጋጀዉን ቅጽ በመሙላት ይቀርባል።"

**(46)** የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.1.3 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.1 ስር ተጨምሯል፡፡ ንዑስ አንቀፅ 16.2.2.1.3 የነበረው ንዑስ አንቀፅ 16.2.2.1.4 በሚል ተሸጋሽጓል፡፡

"16.2.2.1.3 የምርት ገበያው በሚያዘጋጀው የስራ ማኑዋል በሚወሰነው መሰረት ምርት ገበያው በአንቀጽ 16.2.2.1.2 መሰረት ገዥ የቅሬታ አቤቱታ እንዳቀረበ ቅሬታ ስለመቅረቡ ሻጩን በጽሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ ወዲያዉኑ ማሳወቅ አለበት፡፡ ሻጩ ወይም ወኪሉ ገዥ ምርቱን ከምርት ገበያው ከማውጣቱ በፊት በአንቀጽ 16.2.2.8.2 መሰረት ናሙና ሲያስወስድ መገኘት ይችላሉ፡፡ የሻጩ ወይም የወኪሉ አለመገኘት ስራዉን አያስቆምም፡፡ በሚጨረሻም ምርት ገበያው የባለሙያ ወሳኔ ወጤቱን ለሻጩ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡"

**(47) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.1.3 የነበረው ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.1.4 በሚል ተሸጋሽጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡**

"16.2.2.1.4 የቡና ጥራት ቁጥጥር ማእከልም ቅሬታዉ በደረሰዉ በሦስት የስራ ቀናት ወስጥ የሚከተሉትን ይፈጽማል።

ለ. ቅሬታዉን የሚያታዉን የባለሙያዎች ቡድን ከራሱ ሰራተኞች ሦስት እንዲሁም ከምርት ገበያዉ እና ከቅሬታ አቅራቢዉ ከእያንዳንዳቸዉ አንድ አንድ ባለሙያዎችን በመጥራት አምስት አባላት ያለዉ ጉባኤ ያደራጃል። በሚሆኑም ቅሬታ አቅራቢዉ ወይም ምርት ገበያዉ ባለሙያ ለመመደብ

ካልቻለ ወይም ካልፈለገ እንደነገሩ ሁኔታ የቡና ጥራት ቁጥጥር ማእከል አንድ ወይም ሁለት ተጨማሪ ባለሞያ/ዎች በመመደብ ጎዶሎ ቁጥር ያለው የባለሞያዎች ጉባኤ ያደራጃል፣ እንዲሁም"

**(48) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.2 እና 16.2.2.3 እንደሚከተለዉ ተሻሽለዋል፤**

"16.2.2.2 ቡና ጥራት ቁጥጥር ማእከልም ከላይ በንዐስ አንቀፅ 16.2.2.1.4(ሀ) መሠረት ናሙዉ እንደደረሰዉ በተመደበው ሰራኛዉ አማካኝነት በናሙዉ ላይ ያሉትን ምልክቶች'የከረጢቶች ቁጥር'የመኪና ታርጋ ቁጥር እና የማጠን ማሜልከቻ ጽሁፎች ካሉ ጽሁፎቹን በማንሳት ከእራሱ ውጭ ሌላ ሰው የሚረዳወን ምልክት ማስጠት አለበት። የዚህ ተግባር ዓላማ የቡናዉ ባለቤት ማንነት ለባለሞያዎቹ እንዳይታወቅ ለማድረግ ነው።"

16.2.2.3 የጥራት ባለሞያዎች ጉባኤ

በንኡስ አንቀጽ 16.2.2.1.4 (ለ) በተገለጸዉ መሠረት ከምርት ገበያዉ እና ከቅሬታ አቅራቢዉ ከእያንዳንዳቸዉ አንድ አንድ ባለሞያዎች እና ከቡና ጥራት ቁጥጥር ማእከልም ሦስት የጥራት ባለሞያዎች የተካተቱበት አምስት አባላት ያሉት ያለመግባባት በተነሳ ጊዜ የሚሰየም ጊዜያዊ የጥራት ባለሞያዎች ጉባኤ (ከዚህ በኋላ "ጉባኤው" እየተባለ የሚጠራ) ይኖራል።"

**(49) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.5.1 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፤**

"16.2.2.5.1 የቡና ጥራት ቁጥጥር ማእከል ያለመግባባት የተነሳበትን የቡና ናሙና ከሌሎች ሁለት ያለመግባባቱ ከተነሳበት ቡና ጋር አንድ አይነት ደረጃ ካላቸዉ ማስመሰያ የቡና ናሙናዎች ጋር በማጀብ ለጉባኤዉ ያቀርባል። የናሙናዎቹ ምርመራ በአንድ ላቦራቶሪ በአንድ ጊዜ በሦስት ሰዓታት ወስጥ ተደርጎ ማጠናቀቅ ይኖርበታል።"

**(50) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.7 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፤**

"16.2.2.7 በባለሞያ ወሳኔ ሂደት ወቅት የባለጉዳዮቹ ግዴታ

የምርት ገበያዉ እና የቅሬታ አቅራቢዉ ባለሞያዎች በጥራት ባለሞያዎች ጉባኤ የመሳተፍ መብታቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባኤዉ አንዴ ምርመራውን ከጀመረ በኋላ ባለጉዳዮቹ ወደ ቡና ጥራት ቁጥጥር ማእከል መሄድ የለባቸውም።"

**(51) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.8.1 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፤**

"16.2.2.8 በክርክር ላይ ያለዉ ቡና አያያዝ

16.2.2.8.1 ክርክሩ በአቅራቢ እና በምርት ገበያዉ መካከል በሚሆንበት ጊዜ በቀረበው የጥራት/ደረጃ ክርክር ላይ የምርት ገበያው አግባብነት ያለው የስራ ክፍል ወሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ላለመግባባቱ ማነሻ የሆነው ቡና በመኪናዉ ላይ እንደተጫነ የምርት

ገበያዉ ማዛዘን ባለበት ግቢ ዉስጥ እንደቆመ ይቆያል። በዚህ ጊዜ ምርት ገበያው በጉዳዩ ላይ ወሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የምርት ገበያዉ በናዉን ሚልሶ ማሸግ ይችላል።

(52) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.8.2 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.8 ስር ተጨምሯል፡፡ ንዑስ አንቀፅ 16.2.2.8.2 የነበው ንዑስ አንቀፅ 16.2.2.8.3 በሚል ተሸጋሽጓል፡፡

16.2.2.8.2 ክርክሩ በአቅራቢ እና በምርት ገበያዉ መካከል በሚሆንበት እና ክርክሩ ወደ በና ጥራት ቁጥጥር ማእከል በሚሄድበት ጊዜ በቀረበው የጥራት/ደረጃ ክርክር ላይ የቡና ጥራት ቁጥጥር ማእከል ወሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ላለመግባባቱ ምክንያት የሆነው ቡና በምርት ገበያዉ ማዛዘን የሚቆየ ሲሆን አቅራቢው የቡና ጥራት ቁጥጥር ማእከል ለምርቱ በሚሰጠው የጥራት ደረጃ ወሳኔ መሰረት በምርት ገበያው ማዛዘን ያከማቸዉን ምርት ለመቀበል የተስማማ መሆኑን በምርት ገበያው የሚዘጋጀዉን ግዴታ መግቢያ ሰነድ መፈረም ሚጋገጥ አለበት፡፡ የቡና ጥራት ቁጥጥር ማእከል በጉዳዩ ላይ ወሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የምርት ገበያዉ ቡናዉን ሚልሶ ማሸግ ይችላል።"

**(53) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.8.2 የነበረው ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.8.3 ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡**

"16.2.2.8.3 ገዥው ቡናዉን ተረክቦ በናው መኪና ላይ ከመጫኑ በፊት ምርት ገበያው ማዛዘን ወስጥ እያለ ገዥው ወይም ተወካዩ እና የቡና ጥራት ቁጥጥር ማእከል ሰራተኛ በተገኙበት ከእያንዳንዱ መደብ አጠቃላይና ወካይ የሆነ አንድ ኪሎ ግራም የሚሆን ቡና ከያንዳንዱ ጭነት ላይ በምርት ገበያው ናሙና ሚወሰድ ይችላል፡፡ ናሙናው በሁለት ተከፍሎ አንዱ በምርት ገበያው የሥራ ናሙና፣ ሁለተኛው ክፍል በምርት ገበያው ደህንነቱ በተጠበቀ እቃ በጥንቃቄ የሚቀመጥ ሆኖ በምርት ገበያዉና በቡና ጥራት ቁጥጥር ማእከል የተመደበ ሰራተኛ በጋራ የሚዘጉት ዋቤ የጭነት ናሙና ይሆናል፡፡ በምርት ገበያዉና በቡና ጥራት ቁጥጥር ማእከል የተመደበ ሰራተኛ በጋራ የሚዘጉት ዋቤ ናሙና እስከ 10 ቀን ድረስ በምርት ገበያው ተጠብቆ መቆየት አለበት፡፡"

**(54)** የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.8.4 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.8 ስር ተጨምሯል፡፡ ንዑስ አንቀፅ 16.2.2.8.3 እስከ 16.2..8.6 የነበሩት ንዑስ አንቀጾች 16.2.2.8.5 እስከ 16.2..8.7 በሚል ተሸጋሽጓል፡፡

"16.2.2.8.4 ገዥው በአንቀጽ 16.2.2.8.3 ላይ በተገጸው ሚልኩ ናሙና ካላስወሰደ በጥራቱ ላይ ቅሬታ ማቅረብ እና የሶስተኛ ወገን የደረጃ ምርመራ እንዲደረግ ማጠየቅ አይችልም፡፡"

(55) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.8.3 የነበረው 16.2.2.8.5 በሚል ተሸጋሽጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"16.2.2.8.5 ቡናው በገኘው የንግድ ቦታ እንደደረሰ ገኘው በአንቀጽ 16.2.2.8.3 ማስረት ናሙና ያስወሰደ ከሆነ እና በደረጃው ላይ ቅሬታ ካለው ቡናውን ከምርት ገበያው መጋዘን ካነሳበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት ቀናት ወስጥ የቡናውን የጥራት ደረጃ በተማከከተ ጉዳዩን ለቡና የጥራት ቁጥጥር ማእከል በማቅረብ ሊቃወም ይችላል::"

(56) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.8.4 የነበረው 16.2.2.8.6 በሚል ተሸጋሽጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"16.2.2.8.6 አለመግባባቱ በገኘው እና በምርት ገበያው መካከል ከሆነ የባለሞያ ወሳኔ አሰጣጡ በንዑስ አንቀፅ 16.2.2.8.3 ተወስዶ በምርት ገበያው ለቡና ጥራት ቁጥጥር ማእከል የተላለፈውን የማስረያ ናሙና መሠረት በማድረግ የሚከናወን ይሆናል::"

(57) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.8.5 የነበረው 16.2.2.8.7 በሚል ተሸጋሽጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"16.2.2.8.7 የባለሞያ ወሳኔ አሰጣጡ በንዑስ አንቀፅ 16.2.2.8.3 ስር የተጠቀሰውን ዋቤ ናሙና ማስረት በማድረግ ይከናወናል::"

**(58) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.9 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡**

"16.2.2.9 የይግባኝ መብትን ስለመተዉ

በክርክሩ ሂደት የቡናው ጥራት ደረጃ ወርዷል ለማለት የምርት ገበያው በቂ ምክንያት ሲኖረው እንደገና ለቡናው ደረጃ የማስጠት መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ ደንብ ማስረት በጥራት ክርክር ላይ የሚሰጥ የባለሙዎች ወሳኔ የመጨረሻ እና አስገዳጅ ነዉ፡ ባለጉዳዮቹ (የምርት ገበያዉ እና አባሉ) በማንኛውም ሁኔታ ከቡና ጥራት ቁጥጥር ማእከል የባለሙዎች ወሳኔ ላይ ይግባኝ ወደየትም መወሰድ አይችሉም፡"

(59) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.10 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2 ስር ተጨምሯል፡፡ ንዑስ አንቀፅ 16.2.2.10 እስከ 16.2.2.11 የነበሩት ንዑስ አንቀጾች 16.2.2.11 እስከ 16.2.2.12 በሚል ተሸጋሽገዋል፡፡

16.2.2.10 የቡና ጥራትና ቁጥጥር ማእከል ወሳኔን በድጋሚ ስለማየት

i) ከላይ በንኡስ አንቀፅ 16.2.2.9 የተደነገገው ቢኖርም የቡና ጥራትና ቁጥጥር ማእከል ወሳኔ ምርት ገበያው ለምርቱ ከሰጠው የጥራት ደረጃ ሁለት እና ከሁለት ደረጃ በላይ ልዩነት እንዳለው ካሳዩ የሚቀርብ አቤቱታን የቡና እና ሻይ ልማትና ግብይት ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ ማስረት በድጋሚ እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

(60) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 16.2.2.11 የነበረው 16.2.2.12 በሚል ተሸጋሽጎ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፤

"16.2.2.12 ናሙና

ለባለሙያ ወሳኔ ሲባል ወደ በና ጥራት ቁጥጥር ማእከል ከተላከዉ የበና ናሙና ወስጥ ለቅምሻ ፍጆታ ያልዋለዉ የባለሙያ ወሳኔ ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ምርት ገበያዉ ማዛዝን ይመላሳል።"

3. **ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን**

በደንቡ ንዐስ አንቀጽ 21 (1) ማስረት ይህ ደንብ በባለሥልጣኑ ከጸደቀ ከአስራ አራተኛው ቀን በ|ላ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

**በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ቦርድ ሚያዝያ 21 ቀን 2012 ዓ.ም በአዲስ አበባ ጸደቀ፡፡**